# ጉዳዩ ዶሮ ብታልም ጥሬዋን ነው

ዮናስ 04-03-18

የውጭ ግንኙነት እንቅስቃሴያችን የተመሰረተው በአገር ውስጥ ድህነትና ኋላቀርነትን በማጥፋት ትግል ላይ ነው። ይህ በጠንካራ ህዝባዊና አገራዊ ጥቅምና አተያይ ላይ የተመሰረተው የውጭ ግንኙነት አቅጣጫ ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ የላቀ ተቀባይነት እንዲኖራትና አገራዊ ጥቅሟንም እንድታሰፋ ያስቻላት ነው። ይህ ከቅርብ ጎረቤቶች ጀምሮ ከመላው አፍሪካ ጋር፣ ከዚያም አልፎ ከልዩ ልዩ የዓለም ማህበረሰቦች ጋር በተፈጠረው መልካም ግንኙነትና ለዓለም ሰላም ባበረከትነው አስተዋፅኦ እንዲሁም በገነባነው መልካም አተያይ  የተገኘ ውጤት ነው።

የቅርብ ጎረቤቶቻችን  ኢትዮጵያ የሰላማቸው፣ የእድገታቸውና የተጠቃሚነታቸው ምንጭ ልትሆን እንደምትችል የተገነዘቡበት ግንኙነት ስለመፍጠራችን አለም ታላላቅ በሆኑ መድረኮች ላይ ሳይቀር አጨብጭቦ የመሰከረልን እውነታ ነው። ከኤርትራ መንግስት በስተቀር፣ ከሶማሊያ እስከ ኬንያ፣ ከሰሜን ሱዳን እስከ ደቡብ ሱዳንና ጅቡቲ  ካሉ አጎራባች አገሮች ጋር የፈጠርነው መልካም ግንኙነት በአገራችን በጎ እሳቤ ላይ የተመሰረተ ነው።

በራሱ በኤርትራ መንግስት ተናዳፊ ባህሪ ምክንያት የተፈጠረው ምስቅልቅልም በወሳኝነት የኢትዮጵያ ነው የማይባል ድክመት የፈጠረው ነው። በመሆኑም ከኤርትራ መንግስት በስተቀር የኤርትራን ህዝብ ጨምሮ ከሁሉም አጎራባች መንግስታትና ህዝቦች ጋር ያለን ወዳጅነት ጠንካራ መሆኑም የአለምን አሰላለፍ ወደኛ መቀልበስ አስችሏል። ኢትዮጵያ ለችግራቸው የምትደርስ አገርና ፅኑ አጋር መሆኗን የሚቀበሉ አገሮችና ህዝቦች የተበራከቱትም ለዚህ ነው።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ልማት፣ ሰላምና ዴሞክራሲ ይጠናከር ዘንድ የተጫወተችው ሚናም ሌላኛው ምክንያት ነው። ከምንም ነገር በፊት ኢትዮጵያ ራሷን በማንም ላይ የምትጭን ሸክም ላለመሆን ያደረገችው እንቅስቃሴ ለፈጣንና ህዝብ የሚጠቀምበት እድገት ያበቃት መሆኑ፣ በአፍሪካውያን ዘንድ በጎ ምሳሌ ሆና እንድትታይ አድርጓታል። ከመቶ ዓመታት በፊት በቅኝ ገዥዎች ላይ በተጎናፀፈችው አንፀባራቂው የአድዋ ድል ለመላ አፍሪካውያን የኩራት ምንጭ የነበረችው ኢትዮጵያ፣ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በ21ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ ደግሞ ስኬታማ የኢኮኖሚ ሞዴል ተደርጋ መታየት ጀምራለች። በዚህ ላይ አፍሪካውያን ወገኖቻችን በሚቸገሩበት ጊዜ ሁሉ ግንባር ቀደም ደራሽ ለመሆን ችላለች።

ከሩዋንዳ እስከ ቡሩንዲ፣ ከሱማሊያ እስከ ላይቤሪያ፣ ከደቡብ ሱዳን እስከ ሰሜን ሱዳን ባሉ የግጭት አጋጣሚዎች ሁሉ ከማንም በፊት ደርሳ ከባዱን ሸክም ለመሸከምና አገራቱን ከግጭት የፀዱና የተረጋጉ ለማድረግ ቁልፍ ሚና ተጫውታለች። በዚህም ላይ እንደኔፓድና የአፍሪካ ህዳሴ የመሳሰሉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ግንባር ቀደም ተሳታፊ መሆኗ፣ በዓለም አደባባይ የአፍሪካውያንን መብትና ጥቅሞች ማዕከል ባደረገ ጥብቅና መሟገቷ ሁሉ ተዳምሮ አገራችን የአፍሪካውያንን ልባዊ ድጋፍና ፍቅር እንድታተርፍ ከማስቻሉም በላይ በአለም መድረክ ፊት ሞገስ እንድታገኝ አስችሏታል።

ከአፍሪካውያን ጋር በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ለመንቀሳቀስ ዝግጁ መሆኗ፣ በኢነርጂ ልማትና በድንበር ተሻጋሪ ወንዞቿ አጠቃቀም ላይ በተከተለችው የአርቆ አስተዋይነት መንገድ በተለምዶ በጠላትነት ይመለከቷት ከነበሩ መንግስታት ሳይቀር የተሻለ ግንኙነት ልትፈጥር መቻሏ በእርግጥም  የአለምን አሰላለፍ ወደኛ መቀልበስ ቢያስችላት ቢያንስባት እንጂ አይበዛባትም። ከምንም ነገር በላይ የኢትዮጵያንና የአፍሪካ መብትና ጥቅሞች ማዕከል በማድረግ፣ በዚህ ረገድ የተፈፀሙ ታሪካዊ ስህተቶች እንዲታረሙና እንዳይደገሙ በመከላከል፣ በእነዚህ ምትክ ዓለም

አቀፍ ማህበረሰብ ለራሱ ሲል ከእኛ ከአፍሪካውያን ጋር በቀና መንፈስ እንዲተባበር ሃገራችን ያደረገችውም ከፍተኛ ጥረት የተሳካ ሆኗል። ይህ ጥረት ኢትዮጵያ ከነባርም ሆነ ከአዳዲስ ጎራዎች ነፃነቷን አስጠብቃ የማንም ተላላኪ ሳትሆን በመንቀሳቀሷና በዚህም ደግሞ ለጋራ ፍትሃዊ ጥቅሞች በመሰለፍ ረገድ አስተማማኝ አጋር መሆኗን በማረጋገጧ ከሁሉም ልዕለ ሃያላን ሳይቀር በጎ ግንኙነት ለመመስረት ያስቻላት ድንቅ ስኬት ነው።

ከአውሮፓ ህብረት እስከ ተባበረው የአሜሪካ መንግስት፣ ከሩሲያ እስከ ቻይና፣ ከጃፓን እስከ ኮሪያ ድረስ ካሉ አገሮች ጋር መልካም ግንኙነት ፈጥራለች። ከመካከለኛው ምስራቅ እስከ ደቡብ አሜሪካና አውስትራሊያ ድረስ ካሉ አገሮች ጋር በበጎ ምልከታ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ገንብተናል። አሁን ግን ይህን በጎ እይታና ምልከታ ይልቁንም ሃገራዊ ጥቅም የሚፈታተኑ ፍንጮች መታየታቸው አሳሳቢ ሆኖብናል። በእርግጥ እነዚህ አደጋዎች ከሰሞኑ ኢህአዴግ የግንባሩን ሊቀመንበር መምረጡን ተከትሎ የተረጋጋን የሚመስል ሁኔታ ቢፈጠርም የመረጋጋቱ መንስኤ ሲነሳ ከነበረው ጥያቄ አኳያ ሲመዘን ምክንያታዊ አይደለምና ግና አስቸጋሪ ሁኔታዎች ከፊታችን እንደተደቀኑ ማመን ያስፈልጋል። የሚያስፈልገን አላቂ መፍትሄ እንጂ ግለሰብ ላይ የተመሰረተ መረጋጋት ከላይ ለተመለከቱት ሃገራት እና አህጉራት ከሚዛን የሚገባ አይደለም። እነዚህ ሃገራት የዋስትናቸው ምንጭ ሊያደርጉን የሚችሉት ከግለሰብ ባሻገር በሆነ ቁመና ላይ እስከተገኘን ድረስ ብቻ ነው።

ያሳለፍናቸው ሶስት አመታት የእለት ተለት ዜናዎች ዜጎች ከመኖሪያ ቀዬአቸው መፈናቀላቸውን የተመለከቱና የሕይወት መጥፋትና የአካል ጉዳት ላይ ያጠነጠኑ ነበሩ፡፡ በብዙ አካባቢዎች የዜጎች በሰላም ወጥቶ የመግባት እንቅስቃሴ ሲገደብ ተስተውሏል፡፡ ከፍተኛ ሀብት የወጣባቸው ትልልቅ ፋብሪካዎችና መሠረተ ልማቶች በሴኮንድ ወደ አመድነት ተቀይረዋል፡፡ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚደረገው የሸቀጦች ዝውውር ተስተጓጉሏል፡፡ መንግሥትም አገሪቱን በመደበኛው የሕግ

ማስከበር ሥርዓት ማስተዳደር የማይችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በአገሪቱ ያጋጠመውን ቀውስ ተከትሎም በመላ አገሪቱ ተግባራዊ የሚሆን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጇል፡፡ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከታወጀ በኋላም ቢሆን የዜጎች ሕይወት ጠፍቷል፡፡ ንብረት ወድሟል፡፡ የዜጎች የመንቀሳቀስ መብት ተገትቷል፡፡ ይህን ሁሉ ጉዳይ ከግለሰብ ምርጫ ጋር ተያይዞ ተሻግረነዋል ብሎ ማሰብ ከየዋህነትም በላይ ጅልነት።ከላይ ለተመለከቱ ጥቅሞቻችን እና ስማችን ግና ከሶስት አመታትም በላይ መስራት ይጠይቀናል። በዚህ ከሻረልንም ተመስገን ነው። ያሳለፍነው ችግርና አሁን ያለንበት አራዳድ በጣም የተሳሳተና ወደባሰውና ወደማንወጣው አዘቅት እንዳይከተን መጠንቀቅ ያሻናል።

በሃገራችን ተፈጥሮ የነበረውና አሁንም ያልለየለት ችግር  ጉዳቱ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለቀጣናውም እንደሆነ ብዙዎች ብዙ ያሉለት ነው፡፡ ከላይ በተመለከተው አግባብ በውስጣችን በፈጠርነው ሰላምና ልማት ባስገኘልን ዝናና ከፍታ ልክ ላለፉት ሶስት አመታት የተዘፈቅንበት ጉዳይ በዚያው ልክ ቀጠናውን ጉዳት ላይ ቢጥለው የሚጠበቅ ሲሆን ግለሰብ ላይ ተንጠልጥለን ሁሉ ነገር አበቃለት ማለታችን እንኳንስ ለቀጠናው ለኛም አደጋው የከፋ ነው የሚሆነው።

በዚህ አረዳድ መሰረት ችግሩን መፍታት ከተቻለ ሃገራችን ረዥም ታሪክ ያላት ከመሆኗ ባሻገር አካባቢውን እንደ ንስር ይዛው ልትነሳ የምትችል ግዙፍ አገር መሆኗ አያጠያይቅም። ከዚያ ባሻገር ያለእውቀትና በፌስ ቡክ አብዮት የተፈጠረውን ችግር በፌስቡክ አብዮት ወደነበረበት ተመልሷል ብሎ ስብከት ቀጠናውን ሃገሪቱን እና ሲነሳ የነበረውን አጀንዳ ሁሉ አፈር ድሜ የሚያስበላና እንደገና ለሌላ ችግር እራስን ማጥመድ ነው የሚሆነው።

አካባቢው መረጋጋት የማይታይበትና ለብዙ ጊዜ ሳይፈቱ የቆዩ ችግሮች ያሉበት ነው፡፡   ደቡብ ሱዳን ያለው ብጥብጥ፣ በሱዳን ያለው አለመረጋጋት፣ የኤርትራና የግብፅ በቀጣናው ያላቸው የመክበብ ዝንባሌ፣ በቀይ ባህር አካባቢ የዓረብ ባህረ ሰላጤ አገሮች የጦር ቀጣና ለመመሥረት

ያለው አባዜና ሌሎች ጉዳዮች ተደማምረው አካባቢው በውጥረት የተሞላ እንዲሆን ማድረጋቸው ሊዘነጋ የማይገባውና ችግራችንንም ሆነ መፍትሄውን ከዚህም አንጻር መቃኘት አስፈላጊ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል፡፡

ኢትዮጵያ እኮ በሶማሊያና በሶማሌላንድ የተስፋ ምድር ተደርጋ የምትቆጠር ታላቅ ሃገር ነች። በቀጣናው ሠራዊቷን ከማሰማራቷ ባሻገር አጀንዳ በኢጋድ ደረጃ ይዛ የማስታረቅ ሥራ የምታከናውንና የምታስተባብር ነች፡፡ በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች የሚሰማራው ሰላም አስከባሪ ኃይልም ሕዝባዊነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ብዙዎች መስክረዋል፡፡ ይኼ ሁሉ የአገሪቱ ሚና በውስጥ ችግር ሳቢያ ጥሩ ሳይሆን ሲቀር ጉዳቱ የሚከሰተው በራስ ላይ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል፡፡

አገሪቱ በውስጥ ችግር በምትታመስበት ጊዜ በዓለም አቀፍም ሆነ በአፍሪካ ደረጃ እየፈጠረች የመጣችው የተሰሚነትና የኃያልነት ሚና አብሮ እንደሚሸረሸር መዘንጋት አይገባም፡፡ አገሪቱ ለዚህ ፈተና የበቃችበት ዋነኛው ምክንያትም፣ ከመልካም አስተዳደር ጋር በተያያዘ በተፈጠሩ ችግሮች ሳቢያ እንደሆነ ከመግባባት ተደርሷል፡፡ እዚህ ለመድረሳችን ምክንያቱ በፊት ከነበረው መንግሥት በተጨማሪ አሁን ያለው መንግሥት ተደራራቢ ችግሮችን በመፍጠሩ በመሆኑም ላይ ህዝብና መንግስት አንድ አይነት አቋም ይዘዋል፡፡ ኢትዮጵያዊነትን ከማጎልበት አኳያም የተሠሩ ሥራዎች አነስተኛ እንደሆኑና ብሔር ተኮር ግጭቶች እንዲፈጠሩ ምክንያት መሆኑም ላይ መግባባት ተፈጥሯል። ይህ ከሆነ ዘንዳ መፍትሄውም ይህንኑ የሚመጥን እና ይህንኑ አጀንዳ ታሳቢ ያደረገ እንጂ የግለሰብ ምርጫን ማድረግ ፍጹም ኢ ምክንያታዊነት ነው።

ኤርትራ አካባቢውን በበላይነት ለመቆጣጠር ትፈልጋለች፡፡ ይህንን የምታደርገው ደግሞ ኢትዮጵያን ለማዳከም ነው፡፡ ግብፅ ከዓባይ ወንዝ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ በቀጣናው ኃያል እንዳትሆን ትፈልጋለች፡፡ ውጤታማ ያልነበረች ቢሆንም ከዚህ በፊት በቀጥታም ይሁን

በተዘዋዋሪ ከኢትዮጵያ ጋር ወደ ጦርነት ገብታለች፡፡ በቀጣናው ይኼን መሰል ጂኦ ፖለቲካዊ ቀውስ ባለበት ሁናቴ ከላይ በተመለከተው አግባብ መፍትሄውን ማሰብ መደምደሚያው ዶሮ ብታልም ጥሬዋን ነው የሚለው ሃገራዊ ብሂል ይሆናል። እያለ የአገር ውስጥን ጉዳይ በአፋጣኝ መፍታት ተገቢ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ከዓባይ ወንዝ ጋር በተያያዘ የግብፅ መንግሥት አገሪቱ ተዳክማ ማየት ይፈልጋል የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ ጅብ በቀደደው ውሻ ይገባል ይባላልና አሁንም ነገሩን አቅልለን ባናየው ይመረጣል። በአገሪቱ የሚታየውን ፖለቲካዊ ቀውስ ተባብሶ ሌላ ኪሳራ ሳያደርስና በቀጣናው ትርምስ ሳይፈጠር ችግሩን አሁንም በመርህና በምክንያታዊነት መፍታት ተገቢ ይሆናል፡፡ ሰሞኑን ተደርገው በነበሩ የሰላም ኮንፈረንሶች ከተሳታፊዎች የተሰማው የችግሮች መዓት ግለሰብ ላይ በመንጠልጠል የሚፈቱ ሳይሆን በመላው ህዝብ ምክንያታዊ ተሳትፎ እና ርብርብ ነው።

በእርግጥ በአገሪቱ የተከሰቱ ችግሮችን በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍለን ስንመለከታቸው አንደኛውና ዋናው የአመራር ቀውስ ቢሆን በየደረጃው ያለውን አመራር ማለት እንጂ አንድ ግለሰብ አለመሆኑን መርሳት አይገባም። ሁለተኛው የኅብረተሰቡ የለውጥ ፍላጎትና ከዚህ ጋር ተያይዘው በሚመጡ ችግሮች ጋር የተያያዙ የመልካም አስተዳደር፣ የፍትሕና ሌሎች ጉዳዮች ሲሆኑ ሦስተኛው ደግሞ የሰላምና የደኅንነት ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ ችግሮች ናቸው፡፡ መፍትሄውም እነዚህን ሁሉ ታሳቢ ባደረገ ትጋት የሚመጣ እንጂ በግለሰብ ላይ ተንጠልጥለን እያለምን ከሆነ እያለምን ያለነው ጥሬያችንን ነው። ጥሬያችንን ማለማችንን እንደ መልካም አጋጣሚ በመቁጠር እጃቸውን ለማስገባት የሚፈልጉ ኃይሎች እንዳሉ ለአፍታም ቢሆን ልንዘነጋ አይገባም፡፡ ምንም ተስፋ ያለው አገር አይደለም ብለው የሚያስቡ፣ በአገሪቱ ብሎም በቀጣናው ቀውስ ለመፍጠር የሚታትሩ ኃይሎች በይፋ ተስተውለዋል፡፡ እነዚህ ሃይሎች ደግሞ እንኳን እንደዚህ ተዝረክርከን ቀርቶ ተጠንቅቀንም የማታመልጣቸው አቅም ያላቸው ኃይሎች ናቸው፡፡

ስለዚህ ዋናው ተጎጂ እኛ እንሆናለን፡፡ የሚያንዣብቡ ጆፌ አሞራዎች አሉ፡፡ እነሱ ያባብሱታል፡፡ ባሳለፍናቸው የሶስት አመታት ብጥብጥ እንኳ ብዙ ብሮችና እጆች የገቡት ከመሰረታዊ ጉዳያችን ርቀን ጥሬያችንን ማለም ስለለመደብን ነው።

ይህ ደግሞ ከኛም አልፎ በአካባቢው የነበረንን መልካም ስምና ተፅዕኖ ያሳጣናል፡፡ ብርሃን መስጠት የምትችል አገር እንዲህ ዓይነት ችግር ውስጥ ገብታ ራሷን ማላቀቅ ሲያቅታት ማየት ያሳፍራል፡፡ ከዚህ እፍረት ለመላቀቅ የሚያስችለው የመፍትሄው መጀመሪያ ደግሞ ጥሬያችንን ከማለም መላቀቅ ነው።